# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 38 ጥር 28 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

"...በተወሰኑ የፖለቲካ መሪዎች ወይንም ድርጅቶች መቀየም ወይንም ማዘን፤ ለነፃነትና ለመሰረታዊ የሰውነት መብታችን የምናደርገውን ትግል እንድንተውና ዝም ብለን በባርነት ለመገዛት እንድንወስን ሊያደርገን ፈፅሞ ልንፈቅድለት አይገባም:: .... "

## ምን ላይ ስንደርስ ነው በቃን የምንለው?

የግንቦት 7 ንቅናቄ በዳላስ በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ
ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ያደረጉት ንግግር
የመጨረሻ ክፍል

(በገፅ 3 ላይ ይመልከቱ)

### ማስታወቂያ

ዛሬ በግንቦት7 ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች ሃገራችን ወደሌላ የአመጽ አዙሪት እንዳትገባ ከምር ተጨንቀን፣ አንቸኩል! ለወያኔ እድል እንስጠው፤ ግድ የላችሁም እነዚህ ሰዎች የእዚችው ሃገር ዜጎች ናቸው ውለው አድረው ለሀገራችን በጎ መመኘታቸው አይቀረም ብለን ብዙዎች እስከሚታዘቡን መሟገታችንን ----ያውቃሉ?

ሸህ ግዜ ቀናውን፣ ሸህ ግዜ የሰላሙን መንገድ ብንመኘው፣ ሸህ ግዜ እረ ተው፣ ይህች ሃገርና ሁላችንም በጥፋት አዙሪት ውስጥ መድፈቁ ይብቃን ብለን ብንማጸን፤ ከእዚህም አልፎ ተርፎ በታሪካችን አድርገን የማናውቀውን፣ ለሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ተነስተን፣ በሃገራችን ላይ የተሰራውን በደል ወደ ጎን አድርገን፣ በነጻነታችን ተደራድረን ለእረቅ ለስምምነት ጉሮሯችን እስኪደርቅ በመወትወታችን ፣ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ያገኘነው ምላሽ፣ እየገዘፈ የሚሄድ ዘረኛነት እብሪትና ንቀት እንደሆነ እርስዎስ ቢሆን ሳይታዘቡት አይቀርም::

እነዚህ ዘረኛ እብሪተኞች ትእግስታችንና ተማጽኗችንን ከፍርሀት የሚቆጥር፣ ያለእኛ ደፋር የለም አንዲሉ አድርጎ የሚያይ በባሩድ ሽታ የሰከረ ህሊና ያላቸው መሆናቸውን እርስዎም እንደኛ ሳይረዱት አይቀርም::

በተደጋጋሚ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ዜጎች ማሰቃየት ማዋረድና ማዋከብ ስራ ብለው ተያይዘውታል:: የቅረቡ ሰለባቸው ቴዲ አፍሮ የሆነበት ምክንያት የሚነሳው ከእዚሁ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ ነው:: በልምና በምልጃ ስለሰላምና እርቅ በመስበክ የለየላቸው አረመኔዎችን ወደ ቀና ጎዳና መመለስ ይቻላል ብለን እኛ በግኑብት ሰባት ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖዎችዎ አናምንም:: ይህንን እምነታችንን የሚጋሩ ከሆነ! ይነሱ ይቁሙ እኔንም በቃኝ ውርደት ብለው ከቆሙቱ ጎን ቁጠሩኝ ይበሉ::

የግንቦት7 ንቅናቄን ሁለ ገብ ትግል ይደግፉ:: ለእዚህ ትግል ማራመጃ ግንቦት ሰባት ይሆን ዘንድ ግንቦት 7 የጀመረውን የገንዝብ ማሰባሰብ ስራ ያግዙ:: ሌላውም እንዲተባበር ያስተባብሩ::

ግንቦት 7 ለፍህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ

ግንቦት7 ለፍትሕ እና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የመጀመሪያውን ጠቅላላ ጉባኤው ባለፈው ቅዳሜ ጥር 23 በተሳካ ሁኔታ ማድረጉን አስታወቀ ። በአውሮጳ ፣በሰሜን አሜሪካ፣በአፍሪካ፤ በእስያ፤ በአውስትራሊያና በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙት አባለቱ የተሳተፉበት ይህ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ ንቅናቄው የሚመራበትንና ተሻሽሎ የቀረበውን ህገ-ደንብ በቋሚነት በማጽደቅ እና እስካሁን በጊዜያዊነት ሲያገለግሉ የነበሩትን የስራ አመራር አባላት፣ ለሚቀጥሉት ሁለት አመታት በቋሚነት እንዲያገለግሉ በምርጫ ለተሰየሙ የንቅናቄው ማእከላዊ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት መተካቱን ንቅናቄው በትናንትናው ዕለት ባወጣው መግለጫ አስታውቋል ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ሁለት የመከላከያ ኢንጂነሮች ወያኔን ከዱ

ደብረዘይት ከሚገኘው የመከላክያ ኢንጂነሪንግ ኮለጅ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪግ በባችለር ድግሪ የተመረቁና በኮምፒውተር ሳይንስ ስፔሻላይዝ ያደረጉ ሁለት ኢንጂነሮች ፤ ለሥልጠና ወደ አውሮጳ ከተላኩ ቦኋላ አስከፊውን የወያኔ አስተዳደር በመተው አውሮጳ ውስጥ ለጊዜው ስሙ ይፋ እንዳይሆን በፈለጉት ሃገር ውስጥ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው ተዘገበ ። እንደ ወታደራዊ ምንጮቻችን ዘገባ ወያኔን በመክዳት በአውሮፓ ጥገኝነት የጠየቁት ወጣት የመከላከያ ኢንጅነሮች አንሙት ደመቀ ጸጋዬ እና ንጉሴ ግርማ ቱሉ የተባሉ ናቸው። በተለይ ከምርጫ97 በኋላ በስልጣን ለመቆየት ብቸኛው አማራጭ የጦር መሳሪያ ማግበስበስ እና ወታደሩን እስከአፍንጫው ማስታጠቅ ነው የሚል አስተሳሰብ የሚገፋው ወያኔ ከቼክ ሪፑሊክ በቅርቡ አሳስቶ የገዛውን የታንክ ስቲሙለስ እንዲያጠኑ ነበር ሁለቱን ወጣት የመከላከያ ኢንጅነሮች በከፍተኛ ጥበቃ ስር አድርጎ የላካቸው። ወያኔ የራሴ ዘር ናቸው ከሚላቸው ውጪ የሆኑ መኮንኖች እና ባለሙያዎች ላይ ምንም እምነት እንደሌለው የገለጹት ወታደራዊ ምንጮቻችን በተለይ በራሳቸው እና በችሎታቸው የሚተማመኑ ሀገር ወዳድ መኮንኖችን በአይነቁራኛ እንደሚመለከትና ለተለያዩ ቅጣቶች እንደሚዳርጋቸው ገልጸዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ግንቦት7 የአውሮፓ ህብረት ለፋሽስቱ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያደረገውን የገንዘብ እርዳታ በማውገዝ መግለጫ አወጣ

ግንቦት 7ለፍትህ ለንፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የአውሮፓ ህብረት ለዘረኛና አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ የሁለት መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ዩሮ እርዳታ ማድረጉን አምባገነንነት በኢትዮጵያ እንዲቀጥል ማበረታታትና በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት አይነት እርምጃ ነው ሲል ለወያኔ የተሰጠውን ችሮታ ተቃውሞ መግለጫ አወጣ።

የ ግንቦት 7መግለጫ፤በአዲስ አበባ የነገሰው ጨቋኝ ቡድን በዜጎቹ እና በነጻ ማህበራት ላይ በሚወስዳቸው የእብሪት እርምጃዎች ከአለማአቀፉ ማህበረሰብ ከፍተኛ ውግዘት እየደረሰበት ባለበት በዚህ ሰአት እርዳታው መሰጠቱ የአውሮፓ ህብረት ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ፤ ለአለም አቀፍ ተደማጭነት ላላቸው የሰብአዊ መብት ተሟጓቾች እና ጉልህ ቁጠር ላላቸው የአሜሪካና የአውሮፓ ህብረት የህግ አውጪዎች ተቃውሞ ያለውን ፍጹም ደንታ ቢስነት ያሳያል ብሎዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ነፃነት ሲሉ ፣ ነፃነት ስንል

“ነፃ ያልወጡ ነፃ አውጪዎች” ፣ ጠባብ ብሄርተኝነትን እንደ ነፃነት፣ ጎጠኝነትን እንደ አርነት አምነውና አሳምነው፣ የእናታቸውን እቅፍ ያልጠገቡ እረኞችን አስታጥቀውና አስከረው ከምኒሊክ ቤተ መንግስት ከገቡ እነሆ 18 አመታት ሊያስቆጥሩ ሶስት ወራት ብቻ ቀራቸው ። በነዚህም 18 አመታት “ማንጁስ” የሚሏቸውን ህፃናት ተጋዳዮች በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ አስተምረውና ለድህረ-ምረቃ ትምህርትም አውሮፓ ድረስ ልከው፣ ከላይ እስከታች በወያኔ የተዋቀረ መንግስታዊ ስርአት አደራጅተው ፣ በአንድ ጎጥ የበላይነትና ገዢነት መሰረት ሃገርን ያህል ነገር እናስተዳድራለን ብለው ደፋ ቀና ይላሉ ። ለነርሱ የነፃነት ትርጓሜው ሌላ ሳይሆን፣ ያው ከበረሃ ጀምረው የተዋደቁለት የአንድ ጎጥ የበላይነት ነው ። ዘረኝነት ነው ።

እኛ ነፃነት ስንል፣ ሰው በሰብእናው ቅዱስ ፣ ንኡድ ፣ ከፈጣሪው የሚሳተፈው ሃያል የመንፈስ ጉልበት ያለው፣ ስለሆነም ወደፈለገበት ለማሻቀብ የማንም ፈቃድና ይሁንታ የማያስፈልገው፣ የራሱን አለም የመፍጠር ክህሎት ያለው፣ የፍጥረታት ሁሉ መቋጫ አድርገን ነው የምናየው ። ከዚህ ጥልቅ ግንዛቤም ስለምንነሳ፣ የነፃነት ርዕይ አመለካከታችን በግለሰቡ ፍፁም ነፃነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ለማህበረሰቡም ሆነ ለመንግስት የተሰጡ መብቶች፣ ግለሰቡ ከሌሎች ጋር ለሚያደርገው መስተጋብር አስፈላጊ ናቸው ብሎ የተቀበላቸውን የመብት ግድቦች፣ ከራሱ ላይ ቀንሶ የሰጣቸው እንጂ ፣ በተገላቢጦሽ ፣ መብቱን ከመንግስትም ሆነ ከማህበረሰብ የሚቀበል አለመሆኑን ከማመን የሚመነጭ ጥልቅ ውቅያኖስ የተቀዳ ነው፣የነፃነት እይታችን ።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የነፃነት መሰረት የኢትዮጵያ ዜጎች ናቸው ። የእያንዳንዱ ዜጋ መብት መከበር፣ የሀገሪቷን ክብርና የኢኮኖሚዋንም ግስጋሴ እንደሚያመጣ እናውቃለን ። አንድ የፖለቲካ ንቅናቄ የዜጎቹን መብት ማክበሩም የሚታወቀው፣ በመጀመሪያ የንቅናቄውን አባላት መብት ያከበረ እንደሆን ብቻ ነው ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሁሉንም አይነት የአደረጃጀት መልኮችንና፣ ሁሉንም አይነት የትግል ግብአቶችን የሚከተል ቢሆንም፣ የአባላቱ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉባቸውን ማሳለጫ መንገዶች ሁሉ ከመፈተሽ ወደኋላ ብሎ አያውቅም ። ለዚህም ህያው ምስክር የሚሆነው፣ ድርጅቱ ገና የዘጠኝ ወር ብላቴና ቢሆንም፣ በዚህ አጭር እድሜ ፣ ሶስት ጊዜ የአባላት ኮንፈረንስ ማካሄዱና ፣ የንቅናቄውም መሪዎች በአባላት ምርጫ እንዲመረጡ ለማድረግ መቻሉ ነው ። በቅርቡ በተደረገውም የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የአባላት ኮንፈረንስ፣ አዲስ አባላት በነባሩ አመራር ላይ የተጨመሩ ሲሆን፣ አመራሩ ትግሉን ለማጎልበት የሚያስችለው ከበድ ያሉ ሃላፊነቶችም እንዲሰጠው ተደርጓል ።

ማንኛውም የፖለቲካ ንቅናቄ ፣ የውልደት፣ የእድገትና፣ የለውጥ ሂደትን መከተሉ የግድ ነው ። ንቅናቄያችንም ከፅንስ ወደ ውልደት፣ ብሎም በእጅና እግሩ ከመዳህ አልፎ ፣ ቆሞ ለመራመድ ወደመውተርተር እየደረሰ ነው ። በጠላት አፈና ወይም በውስጡ በሚኖር ሾኬ ሊወድቅ የሚችልበትን የአደጋ ዘመን አልፏል ብለን እናምናለን ። ስለሆነም የአባላቱን ቁጥር ለመጨመርና፣ በመስራቹ አስኳል ዙሪያ ጠንካራ ጋሻ ለማቆም ወስነናል ። የነፃነት ንቅናቄያችን አባላት እንድትሆኑ ጥሪ ልናደርግላችሁ እንወዳለን ። በድረ-ገፃችን፣ ወይም በአባልነት የምትገምቷቸውን ዜጎች በመጠየቅ፣ ዛሬውኑ ተቀላቀሉን ። የዳር ተመልካች ሆናችሁ “ይህን እንዲህ ቢያደርጉት” ብላችሁ ከመጨነቅ፣ በአባልነት ተቀላቅላችሁ “እንዲህስ ብናደርገው” ለማለት ድፈሩ ። ዘረኞቹን በርዕያችን ጥልቀት፣ በነፃነት ጥማታችን ሃራራ እንበልጣቸዋለን ። አንድ የሚበልጡን ነገር ቢኖር፣ እነርሱ የድርጅትን ጥቅም ሲያውቁ፣ እኛ በግለሰብ አርበኝነት ተቀይደን የዝንብ መጫወቻ መሆናችን ብቻ ነው ። የዕውቀት፣ የገንዘብ፣ የሃገር ፍቅር ችሎታችንን አስተባብሮ ለውጤት የሚያበቃን፣ በአላማ የተሳሰረ ድርጅት ብቻ ሲኖረን ነው፣ የዘረኝነትን ሰንኮፍ ከስሩ መንግለን መጣል የምንችለው ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጠንካራ አስኳሉን ፈጥሮ “አንኳኩ ይከፈትላችኋል” እያለ ነው ። አይዞን ጎበዝ ።

## ግንቦት 7 የፍትህ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ዶ/ር ብርሁኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ ቾኮል ጌታሁንና አቶ ዳንኤል አሰፋ፣ የቀድሞው ጊዚያዊ ማእከላዊ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የነበሩ መሆናቸውን ያስታወሰው ድርጅታዊ መግለጫ ፣ አሁንም ለአዲሱ ኮሚቴ በአባልነት ተመርጠዋል ብሏል። በሌላ በኩል በአደባባይ በግንቦት 7 አባልነታቸው ከሚታወቁት መሃል አቶ ኤፍሬም ማዴቦና አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል፣ የማእከላዊ የስራ አመራር አባላት ሆነው መመረጣቸው ሲታወቅ አንዲት ሴትም የስራ አመራሩ አባል ሆነው መመረጣቸውን ንቅናቄው አስታውቋል።

ጠቅላላ ጉባኤው የንቅናቄውን ሁለገብ የትግል ስልትና የንቅናቄውን ይፋና ህቡእ የሆነ አደረጃጀት ግምት ውስጥ በማስገባት ማእከላዊ አመራሩ ስራን በጥንቃቄና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀበት መንገድ መፈጸም እንዲችል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመወሰንና የማስፈጸም ሙሉ ውክልና ለአዲሱ አመራር እንደሰጠው ሲታወቅ ግንቦት 7 ንቅናቄ የሚያደርገው ትግል በአባላትና በአመራሩ መሃከል በከፍተኛ መተመማን ላይ የተመሰረተ መሆኑን በማስታወስ አመራሩ የተሰጠውን ከፍተኛ ስልጣን በአግባቡ የሚጠቀም እንደሚሆን ያለውን እምነት ገልጾዋል። ይህ የውክልና ስልጣን ንቅናቄው በምስረታው ወቅት ባወጣው ሰነድ ላይ ተመስርቶ፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት ሀገረ-ኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግላቸው ቀጠና አድርገው ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር በጋራ የመስራት መርህ አጥብቆ በመያዝ፣ የመለሰን እብሪተኛ አገዛዝ ለማስወገድ አመራሩ ከተለያዩ ለዴሞክራሲ ከቆሙ ድርጅቶች ጋር ትብብሮችን በአስቸኳይ በመፍጥር እንዲንቀሳቀስ ጠቅላላ ጉባኤው ሙሉ መብት ሰጥቶታል።

መግለጨው ሲቀጥልም ጠቅላላ ጉባኤው፣ የግንቦት 7 ንቅናቄ እስካሁን በሃገሪቱ ወስጥ የሚገኘውን የዘውግ፣ የእምነት፣ የጾታ፣ የእድሜና ሌሎቸም የማህበራዊና የኢኮኖሚ ፍላጎቶች ስብጥር ለማካተት ያደረገውን ጥረት በማድነቅ፣ ወደፊትም ይህ ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች ሁለንተናዊ ስብጥር ግምት ውስጥ ያስገባ፣ አባላትና ደጋፊዎች የማሰባሰቡን ስራ አዲሱ የስራ አመራር በትጋት እንዲሰራ የተለየ መመሪያ ተሰጥቶታል ብሏል ።

ጠቅላላ ጉባኤው ንቅናቄው በአጭር ግዜ ውስጥ ያስመዘገበውን የስራ ውጤት በማድነቅ ነገር ግን ይህ የስራ ውጤት የሁላችንንም ነጻነት ለማስከበር ከሚጠብቀን ስራ ጋር ሲነጻጸር ሊያኩራራን የሚገባ እንዳልሆነ እንዳሰመረበት ተመልክቷል።

ጠቅላላ ጉባኤው ግንቦት 7 በአጭር ግዜ ላስመዘገበው የስራ ውጤት የአባላቱን ታታሪነት ያደነቀ ሲሆን፣ በተለይ ግን በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ለንቅናቄው እጅግ ቀና የሆነ መንፈስ ከማሳየት አንስተው፣ በገንዘባቸው በእውቀታቸው በጉልበታቸው መስዋእትንት በመክፍል ያበረከቱት አስተወጽኦ ንቅናቄው ላስመዘገበው እድገት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ እንደሆነ ግልጽ አድርጎታል።

በመጨረሻም ጠቅላላ ጉባኤው፣ ንቅናቄው ከህዝብ የሚያገኘው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪውን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን በማቅረብ፣ ህዝብ በአመኔታ ለንቅናቄው የሚሰጠው ድጋፍ የመለሰ ዜናዊን አምባገነናዊ አገዛዝ በአጭር ግዜ ውስጥ የመጨረሻው የሃገራችን አምባገነን አገዛዝ እንዲሆን በማድረግ፣ ይህን ብካይ አምራች ስርአት ከሃገራችንና ከሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ትከሻ ላይ ለማውረድ ንቅናቄው መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በሙሉ በስራ ላይ እንደሚያውለው ቃል በመግባት ስብሰባውን አጠናቋል።

## ግንቦት7 የአውሮፓ...(ከገጽ 1 የዞረ)

ግንቦት 7ለፍትህ ለንፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የአውሮፓ ህብረት ለዘረኛና አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ የሁለት መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ዩሮ እርዳታ ማድረጉን አምባገነንነት በኢትዮድያ እንዲቀጥል ማበረታታትና በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት አይነት እርምጃ ነው ሲል ለወያኔ የተሰጠውን ችሮታ ተቃውሞ መግለጫ አወጣ።

የ ግንቦት 7መግለጫ፤በአዲስ አበባ የነገሰው ጨቋኝ ቡድን በዜጎቹ እና በነጻ ማህበራት ላይ በሚወስዳቸው የእብሪት እርምጃዎች ከአለማአቀፉ ማህበረሰብ ከፍተኛ ውግዘት እየደረሰበት ባለበት በዚህ ሰአት እርዳታው መስጠቱ የአውሮፓ ህብረት ለኢትዮድያ ሰፊ ህዝብ ፤ ለአለም አቀፍ ተደማጭነት ላላቸው የሰብአዊ መብት ተሟጓቾች እና ጉልህ ቁጠር ላላቸው የአሜሪካና የአውሮፓ ህብረት የህግ አውጪዎች ተቃውሞ ያለውን ፍጹም ደንታ ቢስነት ያሳያል ብሎዋል።

መግለጫው ሲቀጥልም፤የአውሮፓ ህብረት የተረጋገጠ ልማት የሚመጣው ዜጎች የዴሞክራሲ መብታቸው እና ነጻነታቸው ተጠብቆ፤የህግ የበይነት ሰፍኖ መስራት እና መኖር ሲችሉ መሆኑን ያውቀዋል ካለ በኋላ ኢትዮድያውን ከህብረቱ የሚያስፈልጋቸው በድህው ስም ተሰጥቶ በዘራፊዎች ኪስ ቀልጦ የሚቀር እርጥባን አይደለም ብሏል።በተለይ የኢትዮድያን ህዝብ ህዘን የሚያባብሰው፤ ለደረሱበት ልማት ፣ ብልጽግናና ትብብር መሰረቱ ለሰው ልጅ ነጻነት ታላቅነት ያላቸው ከበሬታ ሆኖ ያስተሳሰራቸው የአውሮፓ ህብረት ሀገራት፤ በኢትዮድያ ለሚፈጸመው ለከት ያጣ ጭቆና አይናችንን ግንባር ያድረገው ማለታቸው እና በአፍሪካ ካሉት አረመኔ ጨቋኞች ግንባር ቀደም ለሆነው እና ከህዝብ በሚደርስበት ተቃውሞ በመንገዳገድ ላይ ለሚገኝ አገዛዝ የሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ የዕርዳታ እጃቸውን መዘርጋታቸው ነው በማለት እርዳታውን አውግዞታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

# ምን ላይ ስንደርስ ነው በቃን የምንለው?

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

**ውድ አንባቢዎቻችን ባለፈው እትማችን ዶ/ር ብርሀኑ "አሁን የምናደርገው ውይይት ግን በነኝህ እምነቶች ላይ ስምምነት ባላቸው ወገኖችና ሰዎች መሀከል የተቀናበረ የጋራ ግፊት ለማድረግ ለምን ይሳነናል የሚለውን ጥያቄ በአጭሩ ለመዳሰስ ነው::" ያሉት ፍሬ ሃሳብ ላይ ማቆማችን ይታወቃል። ዛሬ ከዚህ የሚቀጥለውን ክፍል እንደሚከተለው ይቀርባል።**

## 1. የመተማመን አስፈላጊነትና ለምን እንዳጣነው

በመጀመሪያ ለማንሳት የምፈልገው ልንፈጥር የምንፈልገው ስርአት በመሰረቱ የተወሰነ መተማመንን የሚፈልግ ሆኖ ሳለ እኛ በአብዛኛው እርስ በእርስ የመተማመንን መሰረታዊ የሆነ የሰው ልጆችን የአብሮ መኖር ግዴታ እየተውነው ይመስላል:: ከላይ የጠቀስኩትን አይነት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት በዜጎችና በመንግስት፤ በፖለቲካ መሪዎች በአባላትና በደጋፊዎች ዘንድ፤ እንዲሁም በዜጎች መሀከል የተወሰነ የመተማመን ስሜት መኖር አለበት:: ይህ ከሌለ አይደለም በጋራ ታግሎ ከፋትን ማሸነፍ እንዲሁ በሰላም የሰለጠነ አብሮ መኖርም አይቻልም:: በነገራችን ላይ የመተማመን እጦት እየፈጠረብን ያለውን እክል በትንሹ ግን በጣም ወሳኝ በሆነው የቀጠሮ ማክበር ችግራችን ላይ እንኳዋን በግልፅ ይታያል:: ሁላችንም ሌላው (በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን) በሰአቱ ይመጣል ብለን ስለማናምን፤ በሌሎች ዜጎቻችን ላይ ምንም እምነት ስለሌለን ወይንም እርስ በርሳችን ስለማንተማመን ሁላችንም አንዳንዴ በሚገርም ሁኔታ ከሁለት ሰአት በላይ አርፍደን ቀጠሮ እንመጣለን::

በተለይ በፖለቲካው መስክ የመተማመን ማጣቱ ምንም መሰረት የሌለው ባዶ ስሜት ነው ለማለት አይደለም:: በአንፃሩ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን በደማችን ውስጥ የሰረፀና የማንነታችን አካል የሆነ የማይለወጥ የዘር እርግማን ስላለብን አይደለም:: ከኑሮአችን፤ ከታሪካችን፤ ከልምዳችን ያካበትነው ባህርይ መሆኑን አምናለሁ:: ባለፉት ሶስት አስርት አመታት እንኳዋን እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ብዙ አስከፊ ታሪክ አሳልፈናል:: አሳልፍላችሁአለሁ፤ እኩልነትን አመጣላችሁአለሁ፤ ከፊውዳላዊ ሁዋላ ቀርነት እገላግላችሁአለሁ፤ ያለን መንግስት ቀጥቅጦ ገዝቶናል፤ ልጆቻችንን በልቶብናል፤ የሕሊና ጠባሳ አስቀምጦብን ወድቆአል:: በደልን አውቃለሁ፤ ዴሞክራሲ አመጣለሁ፤ የብሄር እኩልነት አሰፍናለሁ ያለን የተጋዳዮች መንግስት ፍፁም ዘረኛ፤ ፍፁም አምባገነን፤ ፍፁም ትእቢተኛ፤ ፍፁም ቀጣፊ ሆኖ ቁም ስቃያችንን እያሳየን ነው:: ከዚህ ብካይ አምራች ስርአት ይገላግሉናል፤ ዴሞክራሲ ያመጡልናል ብለን ያመንናቸውና ያከበርናቸው የፖለቲካ መሪዎች እርስ በርሳቸው በትንሽ በትልቁ ተባልተው፤ አፍረው አሳፍረውናል:: የሀይማኖት መሪዎቻችን መንፈሳዊ ትምህርቱን ትተው ርካሽ የፖለቲካ መሳሪያ ሲሆኑ ታዝበናል:: የአገር ሽማግሌዎች ያልናቸው ለእውነት መቆም ተስኖአቸው በሀይል ፊት ሲርበደበዱ ተመልክተናል...ወዘተ:: ከዚህ በመነሳትም በመሰረታዊ መልኩ የተሳሳተ ‹ሁሉም አንድ ናቸው፤ ምንም አይታመኑም› የሚል አደገኛ ድምዳሜ ላይ ያደረሰን ይመስላል:: በብዙ ዜጎቻችን ዘንድ የሚታየው የተስፋ መቁረጥ ስሜት በመጠኑም ቢሆን ከዚህ አመለካከት የመጣ ይመስላል::

በእኔ አመለካከት ይህ አይነት ድምዳሜ ቢያንስ በሶስት ምክንያቶች የተሳሳተ ድምዳሜ ነው እላለሁ:: በመጀመሪያ ብዙ ሰዎች ሲያጠፉ ስላየን ሁሉም አጥፊ ነው ማለት አይደለም:: ሁሉም ሰው ለራሱ ጥቅም ብቻ ብሎ የሚንቀሳቀስ፤ ሁሉም ሰው የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት በሰው ላይ ለመረማመድ ምንም የሞራል ደንታ የለውም፤ ሁሉም ሰው ከራሱ በላይ ለሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ ነፃነት፤ የአገር ፍቅር) ስሜት ወይንም ፍቅር የሌለው ነው ብሎ መደምደም የተሳሳተ ነው:: ያ ደግሞ በርግጥ ከሆነ የሚነገረው ስለሌላው ብቻ ሳይሆን ስለራስም ነው ማለት ነው:: ቢያንስ የራሱን ንፁህነት የሚያምን ሰው ሌሎች እንደሱ አይነት ንጹህ ሰዎች መኖራቸውን መጠራጠር አይቻለውም:: እንዲህ አይነት ድምዳሜ ላይ ብዙ ጊዜ የሚደርሱ ሰዎች የአንድን ነገር እውነታ ለማወቅ የሚያስፈልገውን ትንሽም ድካም መድከሙን ጠልተው በስንፍና የጥቅል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚቸኩሉ ወይንም ደግሞ ከዚያም ካለፈ በዚህ አይነት የራሳቸውም ችግር ሊሆን የሚችልን ነገር በጥቅል በሌሎች ላይ ደፍድፈው ሀላፊነታቸውን ላለመወጣት የወሰኑ ሰዎች ነው የሚሆኑት:: የሰው ልጆች እስከሆንን ድረስ ጥሩዎችም መጥፎዎችም አሉብን:: ስንዴውን ከእንክርዳዱ ለመለየት ትንሽ ስራ ይጠይቀን ይሆናል:: መፍትሄው ግን ያንን ስራ መስራት ነው እንጂ ሁሉንም በአንድ ላይ ደብልቆ መውቀጥ አይደለም:: ይህ የሚያመጣው ኪሳራ ግን (ምናልባት እኔ ብቻ ነኝ ንፁሕ ከሚል ግብዝነት ባሻገር) የግለሰቡንም የማህበረሰቡንም ስነልቦና ፍፁም ጨለምተኛነት ውስጥ የሚከትና እራስን ሽባ የሚያደርግ አጉል ነገር ነው:: በዚህ አይነት ስነልቡና ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ለመኖር በጣም ከባድ ነው የሚሆነው:: ከፖለቲካው አንፃርም መተማመን ሳይኖር መደራጀት፤ መደራጀት ሳይኖር መታገል፤ መታገል ሳይኖር ማሸነፍ በፍፁም የሚታሰብ አይሆንም::

ሁለተኛ፤ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ታሪካችንም ቢሆን እንዲህ አይነት ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይደለም:: በመጀመሪያ እስከቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደው ፖለቲካና ይህንንም ፖለቲካ የመሩት ሀይሎች መነሻ እምነታቸው ዴሞክራሲ አልነበረም:: በዚያ መለኪያ ለክተን ይህንን እንደከዱን አድርገን ለመውሰድ አይቻለንም:: ደርግም ሆነ እሱን የተቃወሙ ሀይሎች የታገሉትና የተጋደሉት ግፋ ቢል የኢኮኖሚ እኩልነትን መሰረት ባደረገ ግን ምንም ዴሞክራሲያዊ ኢላማ ለሌለው ርዕዮተ አለም ሲባል እንደነበር አይረሳም:: ስለዚህ በብዙ መልኩ አሁን ለሚደረገው የዴሞክራሲ ትግል ሁላችንም አዲስ ነን:: የስርአቱን የጨዋታ ህግ፤ የሚጠይቀውን የመንፈስ ጨዋነት በቅጡ ባለማወቅ የሚሰሩ ስህተቶችን ሁሉ እየደመሩ የግለሰብ መሪዎች ተአማኒነት ማጣት ውጤት ብቻ አድርጎ መውሰድ፤ በዚህም ተስፋ መቁረጥ ተገቢ ላይሆን ይችላል::ከዚያም በላይ ግን ቢያንስ እራስን አሳልፎ ለአላማ መስጠት፤ ለአገርና ለሕዝብ ካለ ጥልቅ ፍቅር በመነሳት ብቻ (የመጨረሻ አላማው የተሳሳተ ነው እንኳዋን ብንል) ከራስ በላይ ለሆነ ትልቅ አላማ ውድ ሕይወትን ለመክፈል ምንም የማያመነቱ ብዙ ወጣቶችና አዛውንትም ያለፉበት ታሪክ መሆኑን መርሳት የለብንም:: በሌላ አነጋገር የቅርብ ጊዜ ታሪካችን እምነታችንን ሊሸረሽር የሚችሉ ብዙ ነገሮች የተከሰቱበት የነበረውን ያክል በአላማ ፅናት ላይ የተመሰረተ መተማመንም የታየበት ነውና ከክፉው ብቻ ሳይሆን ከደጉም ለመማር መቻል አለብን::

በመጨረሻም ይህ በፖለቲካ መሪዎች የታየው የተአማኒነት ማጣት ሙሉ በሙሉ ትክክልስ ቢሆን ለዚያ የሚሰጠው ምላሽ እንዴት በዋና አላማ፤ ያውም ነፃነትን በሚያክል ትልቅ የተከበረ ነገር ላይ ተስፋ መቁረጥ ይቻላል? በዚህ ተስፋ ተቆርጦ ቢተው ከራስ በላይ ማን ነው የተጎዳው? አንድ ወዳጄ እንዳጫወተኝ ይህ እኮ አንድ በጠና ታሞ ለምርመራ ሀኪም ዘንድ የሄደ ሰው አንድ ሀኪም የተሳሳተ ውጤት ስለሰጠው ሌላ ሀኪም ዘንድ ሄዶ መፍትሄ እንደመፈለግ ሁለተኛ ሀኪምጋ አልሄድም ብሎ፤ ከዘመናዊ የሕክምና እውቀት ጋር ተጣልቶ፤ ቤቱ ተቀምጦ ለመሞት መወሰን አይነት ነው:: በተወሰኑ የፖለቲካ መሪዎች ወይንም ድርጅቶች መቀየም ወይንም ማዘን፤ ለነፃነትና ለመሰረታዊ የሰውነት መብታችን የምናደርገውን ትግል እንድንተውና ዝም ብለን በባርነት ለመገዛት እንድንወስን ሊያደርገን ፈፅሞ ልንፈቅድለት አይገባም:: ይልቁንም መሆን ያለበት እምነታችንን በተቋዋሞችና በራሳችን ንቁ ተሳትፎ ላይ ጥለን፤ የግል ጥቅማቸውን በማስቀደም የጋራ ግባችንን የሚጎዱ ነገሮችን የሚሰሩ መሪዎች ካሉ እነሱን ወይዱ ብለን፤ ሌሎች መሪዎችን መርጠን ወደ ምንፈልግበት የነፃነት ግብ ለመድረስ ይበልጥ ቆርጠን መታገል ብቻ ነው የሚኖረው ትክክለኛ አማራጭ::

## 2. የግለሰብ ሀላፊነትና የመሪዎች/የመንግስት ተጠያቂነት ትስስር በዴሞክራሲ

ሁለተኛው በተግባር ወደፊት ለመሄድ እንቅፋት የሆነብን የሚመስለኝ መሪዎችን ወይንም የፖለቲካ ድርጅቶችን ከራሳችን ማንነት ፍፁም ለይተን ስለምናይ ይመስለኛል:: በሌላ አነጋገር ፖለቲካ እንደጋራ ተግባር በመሪዎችና በአባላት፤ በመንግስትና በዜጎች መሀል የግድ የሚለውን የሀላፊነትና የተጠሪነት ትስስር የሚገባውን አፅንኦት አንሰጠውም:: ይህ ትስስር ቢያንስ ሁለት ቁዋጠሮዎች አሉት:: አንደኛው የመሪዎች ተጠያቂነት ጥንካሬ የሚወሰነው ግለሰቦች ያለባቸውን ሀላፊነት ለመወጣት ከመቻል ካለመቻላቸው ጋር ይያያዛል:: በራሱ ላይ ያለውን ሀላፊነት የሚወጣ ህዝብ ባለበት፤ ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር ጉልበተኞችን ተው ለማለት የሚያስችል መንፈሳዊ ወኔም ይኖራቸዋል:: ማንም እንደፈለገ (እነሱ የመረጡትም ቢሆን) እንዲጋልባቸው አይፈቅዱለትም:: መሪዎችም እንደዚህ አይነት ዜጎች መኖራቸውን ሲያውቁ የተጠያቂነት ስሜት ይይዛቸዋል:: ከማህበረሰቡ ፈቃድ ውጪ አልፎ መሄድ የሚኖረውን አስከፊ ውጤት ስለሚያውቁት ይጠነቀቃሉ:: የዚያኑ ያክል ዜጎች የራሳቸውን ሀላፊነት ሳይወጡ ከመሪዎቻቸው ብዙ ለመጠበቅ የሞራል መሰረትም አይኖራቸውም:: ለዚህ ነው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ጠንካራ መሰረት እንዲኖረው ጥሩ መሪዎች መመረጣቸው ሳይሆን የነቁና መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚችሉ የግል ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች በጣም አስፈላጊ የሚሆኑት:: ባራክ አባማ በተመረጠ እለት ባደረገው ንግግር የአሜሪካ ዜጎች ሀላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ብቻ ሳይሆን የቀድሞው የቴክሳስ አገረ ገዢ ካስገባቸው ቀውስ መውጣት የሚችሉት ማህበረሰቡ በግለሰብ ደረጃ ሀላፊነቱን ከወሰደ ብቻ እንደሆነ በአትኩሮት ያሳሰቡት:: በእዚህ በአሜሪካ ይህ የግል ሀላፊነት ደግሞ አባት ለልጆቹ መፅሀፍ ከማንበብ እስከ ዜጎች በግላቸው ለአገራቸው ያልተከፈለበት ግልጋሎት እስከመስጠት የሚሄድ ነው:: በሃገራችን ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ልንወስድ የሚገባን ሃለፊነት የራሱ ዝርዝር ይኖረዋል:: ሁለተኛ ብዙውን ጊዜ መሪዎች የህዝባቸው ነፀብራቆች ናቸው:: እኔ በከፈልኩበት ታክስ ነውና የምትንቀሳቀሰው ለእኔ

የሚጠቅም ስራ ስራ ብሎ መንግስትን ደፍሮ ለመጠየቅ የሚችል ማህበረሰብ በአብዛኛው የራሱን ታክስ በሀቀኝነት የሚከፍል ዜጎች ያሉበት አገር ነው:: ታክስ መክፈልን የሚያጭበረብር ዜጋ በአብዛኛው ባለበት፤ የዚያኑ ያክል አጭበርባሪ መንግስት ማግኘቱ የሚገርም አይሆንም:: ከኛ የጊዜው ፖለቲካ ጋር ይህ ያለው ትስስር ግልፅ ይመስለኛል:: የፖለቲካ መሪዎችን አይረቡም ብሎ ከማጣጣል በፊት፤ ሁላችንም በጋራ ለገባንበት የመቀመቅ ኑሮ የተወሰኑ አካሎች ላይ ጣት ከመቀሰር በፊት ወይንም ይህ ጣት መቀሰር ትርጉም የሚኖረው እያንዳንዳችን በግላችን ይህንን የኑሮ ሁኔታችንን ለመቀየር በሚደረግ ትግል የሚገባኝን አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ ወይ ብሎ መጠየቅ ይገባል:: የግል ሀላፊነትን ሳይወጡ ሌላውን ማራከስ ቢያንስ ግብዝነት ነው:: በትግሉ ላይ ያለው እንድምታ ግን ከዚያም በላይ ነው:: እኛ በግል ያለብንን የራሳችንን ድርሻ ያለመለገም ካደረስን በትግሉ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ነን ማለት ነው:: ያን ጊዜ መሪዎች ከኛ የጋራ ፍላጎት ውጪ፤ ከጥቂት መሰሎቻቸው ጋር ብቻ በመምከር ወደተሳሳተ መንገድ እንዳይሄዱ ማስገደድ እንችላለን:: ወደምንፈልገውም ግብም በቶሎ መድረስ እንችላለን:: ስለዚህ ሁላችንም ይህን ጥያቄ ለራሳችን እንጠይቅ:: እኔ የሚገባኝን አድርጌአለሁ ወይ? ምንድን ነው ማድረግ የምችለው? ብለን ከልባችን ማድረግ ያለብንን ካደረግንና ለራሳችን ህይወት ሀላፊነታችንን ከወሰድን በምንም አይነት በወያኔ/ኢሕአዴግ አይነት ብካይ መንግስት እንደዚህ ልንዋረድ አንችልም:: ይህን የግል ሀላፊነት ለመጥራት ነው ግንቦት ሰባት "እኔ ለወገኔ" የሚለውን ዘመቻውን የጀመረው::

## 3. ዴሞክራሲ የወሬ ብቻ ሳይሆን የተግባርም፤ የሕልም ብቻ ሳይሆን ሕልምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሞክር ተነሳሽነትንም የሚያጠቃልል መሆኑ::

በሶስተኛ ደረጃ በአጭሩ ለማንሳት የምፈልገው (እዚህ ላይ ግምቴ የተሳሳተ ከሆነ እታረማለሁ) ዴሞክራሲያዊ ስርአትንና ከሱጋር አብሮ የሚሄደውን የዴሞክራሲ መንፈስ ከተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በደንብ ልብ ያለማለት ችግር ይታየኛል:: ዴሞክራሲያዊ መንፈስ ሁልጊዜም ውይይትን፤ ክርክርን ይጋብዛል፤ ያበረታታልም:: ይህ ማለት ግን የድርጊት

መንፈስ አይደለም ማለት አይደለም፡፡ ውይይትና ክርክር አብቅቶ ተግባር የሚጀመርበትና በተግባር ላይ የሚተኮርበት ደረጃ አለ፡፡ ይህን ማድረግ ያልቻለ ስርአት ወይንም ድርጅት አላማው ራሱ የውይይት ክበብ ለመሆን ካልሆነ በስተቀር፤ ህብረተሰብን አስተባብሮ ወደሚፈለግበት ዳርቻ ማድረስ አይችልም፡፡ነፃነት የድርጊት መሳሪያችን ነው፡፡ በነፃነት መነጋገር፤ መከራከር ያለብን ከዚህ ክርክር የሚጨመቅ እውነት ይዘን፤ በዚያ እውነት በመመራት በተግባር መሄድ ወደምንፈልግበት ቦታ እንድንሄድ ነው፡፡ ክርክሩንና ውይይቱን በራሱ እንዳለቀለት ግብ አድርጎ መቁጠርና በዚያ ላይ ብቻ ጊዜ ማጥፋት፤ አንድ እውቀትን በውይይት ካገኙ በሁዋላ ሌላ ጊዜ በዚያ በእውቀት ላይ የሚጨምር ውይይት ይደረግ እንደሆን እንጂ አዲስ ምሳሌ በተፈጠረ ቁጥር በፊት የተረጋገጠውን እውነት አስር ጊዜ እንደገና እየጠየቁ መውቀጥ በምንም አይነት እድገት አያመጣም፡፡ ይልቁንም እንዲህ አይነት አባዜ መሬት ላይ ጠብ የሚል ነገር ሳይሰራ፤ መከራችን እየጨመረ ከመሄድ በቀር አንዲት ጋት እንኳዋን ወደ ግባችን አያስጠጋንም፡፡

ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ግንቦት 7 የኢሕአዴግን ምንነት በተመለከተ፤ ለምን እና እንዴት መወገድ እንዳለበት በአባሎቹ መሀል በሰፊው ተወያይቶበት ግልፅ አቋዋም ይዞአል፡፡ ይህንን አቋዋሙን የሚጋሩ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ፤ ምናልባትም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በዚህ አቋዋም የሚስማማ ይመስለናል፡፡ ይህን አቋዋም ከሞላ ጎደል የሚቀበሉ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ፡፡ አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታና የነመለስን ምንነት በሚመለከት ያልታወቁት ነገሮች፤ በውይይት የሚከሰቱ አዲስ ግኝቶች የሉም፡፡ ስለዚህም ስራችን ይህን እምነታችንን ወደ ተግባር የምንቀይርበትን መንገድ ማመቻቸት ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው ወሬ ይብቃ፡፡ የምናደርገውን ነገር በመሬት ላይ በተግባር ማድረግ እንጀምር፤ እነኝህን እምነቶች የሚጋሩ ሀይሎች በተግባር ስለሚደረገው ስራ እናተኩርና አንድ ላይ ሆነን ይህንን የአበሳ ጊዜ የምናሳጥርበትን መንገድ እናመቻች የምንለው፡፡ ግንቦት 7 እንደ ድርጅት ከአሁን በሁዋላ መመዘን ያለብን በተግባር በምናደርገው እንቅስቃሴ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ለዚያም ተዘጋጅተናል፡፡ እናንተም ለተግባር እንቅስቃሴ ተነሱ ነው ጥሪያችን፡፡ በትግል ሂደት ውጤት ያመጡ ሀይሎች ሁሉም የተግባር ሀይሎች ናቸው፡፡ በወሬ ዴሞክራሲ አይገነባም፡፡ አርቆ ማለምን የዴሞክራሲ መንፈስ ይፈቅዳል፡፡ ሕልምን እውን ለማድረግ በተግባር መንቀሳቀስ ነው የማርቲን ሉተር ኪንግን ሕልም በባራክ ኦባማ ተግባራዊ እንዲሆን የፈቀደው፡፡ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የምናሰፍነው፤ የዜግነት ክብራችንን መልሰን? የምንጎናጸፈው ሁላችንም ባመንንበት የትግል ስልት ተሰልፈን በተግባር ስንንቀሳቀስ ብቻ ነው ፡፡ በወሬ ነፃነት አይመጣም፤ በወሬ አገር አይገነባም፤ በወሬ ክፋት አይፈርስም፡፡ በጫጫታ የፈረሰች እያሪኮ ብቻ ነች ነበር ያለው ደርግ ሲያሾፍ?

**ማጠቃለያ፡**

ይህ የሄድኩበት መንገድ ዙሪያ ጥምጥም ከመሰላችሁና በተለይ ደግሞ ከዚህ ስብሰባ ጋር ያለውን ግንኙነት አደብዝዝቼው ከሆነ ሰብሰብ አድርጌ ዋና መልእክቶቼን ላቅርብና ላብቃ፡፡

1. በአገራችን እየተካሄደ ያለው አስከፊ ሁኔታ መቀየር እንዳለበት ጥቂት የዚህ መንግስት አተፍታፊዎች ካልሆኑ በቀር አብዛኛው ህዝብ የሚያምንበት ነው፡፡
2. ይህን መንግስት የምንቀይረው እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር እንጂ አንድን አይነት አምባገነንነት በሌላ አይነት አምባገነንነት ለመቀየር አይደለም
3. ይህን ሕልማችንን ተግባራዊ ለማድረግ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆንነው ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን የተጠናከረ የጋራ ትግል ለማድረግ ስንችል መሆኑ የሚያጣላ አይመስለኝም፡፡ ሆኖም ይህን ማድረግ እስከአሁን ተስኖናል ስለዚህም አበሳችን እየረዘመና እየጨመረ መጥቶአል
4. ለምን ይህ ሆነ የሚለውን ለማወቅ ብዙ ምርምር የሚጠይቅ ቢሆንም ቢያንስ ለዛሬ ውይይታችን ሶስት ምክንያቶችን አቅርቤአለሁ እነኝህም
   ሀ) መተማመን ማጣት
   ለ) የግለሰብ ሃላፊነትን ከመቀበል መሸሽ እና
   ሐ) ከተግባር ይልቅ በወሬ ላይ ማተኮር
5. እነኝህ ነገሮች መቀየር አለባቸው፡፡ በዚህ ከቀጠልን አበሳችንን ማርዘም ብቻ ነው የምናተርፈው፡፡ ግንቦት 7 እንደ ድርጅት ዜጎች የግል ሀላፊነታቸውን ለመወጣት በተግባር እስከወሰኑ ድረስ፤ ከወሬ ወደ ተግባር እስከተሸጋገሩና በዚህም ድርጅታችንን ለመርዳት ብቻ ሳይሆን እየተከታተሉ ስህተታችንን በማሳየት በትግሉ ቀጥተኛ ተሳትፎ እስካደረጉ ድረስ ድርጅቱ እንደ ድርጅት ሕዝብ ለሚሰጠው እምነት አፀፋውን በተግባር ለማሳየት ቃል ይገባል፡፡ በግንቦት 7 ስር የተሰባሰብነው ሰዎች ልንሳሳት እንችላለን፤ በስልት ደረጃ አንዳንዴ ልናጠፋ እንችላለን፤ ግን ሙሉ ቃላችንን ያለምንም ማመንታት ልንሰጣችሁ የምንችለው በእጅጉ የምንወደውን የራሳችንን ነጻነት፤ የአገራችንን አንድነት፤ የሕዝቡን ነፃነትና ብልፅግና በማስገኘት ከሚገኝ ተሰፍሮ የማያልቅ የላቀ የመንፈስ ደስታ በላይ የምንመኘውና የምንፈልገው ምንም ነገር በአለም ላይ እንደሌለና ይህንንም ለማስገኘት የሚያስችል ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ ወደሁዋላ እንደማንል ነው፡፡

ይህን ሕልማችንን እውን ለማድረግ የናንተን ድጋፍ እንሻለን፡፡ ኢትዮጵያውያን በገፍ የሚሳተፉበት ብዙ መንገድ አለ ብለን እናምናለን፡፡ ይህን ለማመቻቸት በመሬት ላይ ስራ እየሰራን ነው፡፡ በተቻለ መጠን የዚህ መንግስት የአጥፍቶ መጥፋት እርምጃ አገራችንን የማታገግምበት መቀመቅ ውስጥ ከመክተቱ በፊት በአጭር ጊዜ ውጤት መምጣት አለበት ከተባበርንም ለማምጣት እንችላለን ብለን እናምናለን፡፡ የቀየስነው መንገድ የማይሰራ ሆኖ ከመጠን በላይ ጊዜ ቢወስድ፤ ‹እኛ የምንችለውን ሞክረናል፤ አልተሳካልንም፤ ሌሎች ደግሞ በተራቸው ይሞክሩ ብለን ከመድረኩ ለመውጣት ቅንጣት ታክል አናመነታም፡፡ የፖለቲካ ትግል የዘላለም ትግል አይደለም፡፡ መለኪያው ውጤት ነው፡፡ እራሳችንን ለዚህ መለኪያ ተገዢ አድርገናል፡፡ ይህ መንግስት እንደሚወድቅና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በእውናችን እንደምናያት ምንም ጥርጥር የለንም፡፡ ኢላማችን እንዲሳካ ግን የሁሉንም ትብብርና ቀጥተኛ ተሳትፎ እንፈልጋለን፡፡ እርዱን፤ አግዙን ተባብረን ይህን ወራዳ ስርአት እንጣል፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**

# ሁለት የመከላከያ... (ከገጽ 1 የዞረ)

(ከገጽ 1 የዞረ)

ሁለቱ ወጣት የመከላከያ ኢንጅነሮች፡ ወያኔ በመላ ሀገሪቱ በዝረራ በተሸነፈበት የግንቦት 97ቱ ታሪካዊ ምርጫ የቅንጅት ደጋፊዎች ናችሁ ተብለው ድብደባ እና እስር እንደተፈጸመባቸው ተመልክቷል።በመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮሌጅ አይን ያወጣ ዘረኝነት እና ጎጠኝነት እንዳለ የጠቆሙት ምንጮቻችን ካለምንም መስፈርት እና የብቃት መለኪያ ከአንድ አካባቢ በመምጣታቸው ብቻ የፈለጉትን የትምህርት አይነት በብዛት የሚቀላቀሉ እንዳሉ አመልክተዋል።ተማሪው በችሎታው ሳይሆን በዘሩ እና በፓለቲካ አመለካከቱ በሚገመገምበት በዚህ ኮሌጅ በአምስቱ አመት የተማሪነት ዘመናቸው አስቸጋሪ ጊዜ ያሳለፉት አንሙት ደመቀ እና ንጉሴ ቱሉ ፤ በመከላከያ ሚኒስቴርም ስራ ከያዙ በኋላ ማንኛውም የወያኔ አባል ያል ሆነ ሰው ላይ የሚፈጸመው የዘር መድሎ ተጠናክሮ ቀጥሎ ከፍተኛ ክትትል እና ወከባ እንደተፈጸመባቸው ታውቋል።

ወያኔ በብቃት ሳይሆን የእኔ ወገኖች ናቸው ብሎ በኮሌጁ የሚሰገስጋቸው እና የሚያስመርቃቸው ካድሬዎች ምንም የስራ ችሎታ ስለሌላቸው እውቀት የሚጠይቅ ነገር ሲመጣ ካድሬዎቹን ከባለሙያዎች ጋር እያጣመረ እንደሚልክ የጠቆሙት የግንቦት ሰባት ወታደራዊ ምንጮች፤እነ አንሙትንም በከፍተኛ ጥብቃ ሰር አድርጎ የላካቸው የራሱን የተማረ ሰው ማግኘት ቸግሮት እንደሆነ አመልክተዋል።

እንደ ማንኛውም ሀገር ወዳድ የመከላከያ ኢንጅነር እና መኮንን ይህን በህጻናት ደም እጁ የተጨማለቀን ነፍሰ ገዳይ አገዛዝ ጥሎ ለመጥፋት ጊዜ ሲገዙ እና ቀዳዳ ሲፈልጉ የነበሩት ንጉሴ ግርማ ቱሉ እና አንሙት ደመቀ ጸጋዬ አራት ጠባቂዎቻቸው ከተኙበት ሳይነቁ በውድቅት ሌሊት ጠፍተው የፓለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው ተረጋግጧል።የወያኔን ገዳይነት እና ጸረ ኢትዮድያዊነትን ተገንዝበው በተለይ ከአየር ሀይል እና ከመከላከያ ኢንጅነሪንግ የሚከዱ መኮንኖች ቁጥራቸው እየተበራከተ እንደመጣ ተዘግቧል። በርካታ መኮንኖች እና ተዋጊ ፓይለቶች ጊዜ እና ቦታ ሲፈቅድላቸው ወያኔን ከድተው ከታሪክ እና ከህሊና ፍርድ ለመዳን አጥብቀው እንደሚፈልጉ ሲናገሩ የተደመጡት ወታደራዊ ምንጮቻችን ፤ባለፈው አንድ አመት እንኳን በርካታ መኮንኖችና የአየር ሀይል አብራሪዎች አገዛዙን መክዳታቸውን አስታውሰዋል።

ወያኔን የሚከዱ መኮንኖች እና ተዋጊ ፓያለቶች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየተበራከተ መምጣቱ ክፍኛ መረበሽ እና መደናገጥን በወያኔ ሰፈር እንደፈጠር ሲታወቅ፤አገዛዙ በከዱት ተዋጊ ፓይለቶች ላይ በሌሉበት የሞት ፍርድ መፍረዱ ተስፋ መቁረጡን እና መጨነቁን ያሳያል ተብሏል።

በዚህ አጋጣሚ የግንቦት 7 ድምጽ አረመኔውን ገዳይ ብድን ከድተው ከህሊናና ከታሪክ ፍርድ የዳኑትን የመከላያ ኢንጅነሮች እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ በመከላከያ፤በአየር ሀይል፤በደህንነት እና በፓሊስ ሰራዊት ውስጥ ላላችሁ ወንድም እህቶቻችን ሁሉ የነዚህን ባልደረቦቻችሁን ፈለግ በመከተል በናንተ ሥም እናንተ በምትከፍሉት የህይወት መስዋዕትነት የሥልጣን እድሜውን ለማራዘም የሚያልምውን የነ መለስ ዜናዊ፣ በረከት ስምኦንና አቦይ ስብሃት አይነቶቹ ፀረ አገር ሃይሎች ከውንድሞችህ ጋር ደም እንዳያቃቧችሁ በቃችሁ ልትሏቸውና ከህዝብህና ከወገንህ ጎን ተሰልፋችሁ አገራችሁን ከእርስ በርስ ጦርነት፣ ወገናችሁንም ካላስፈላጊ ስቃይ በመታደግ አገራዊ ወገናዊነታችሁን እንድትወጡ ጥሪ ያቀርብላችኋል።

# ግንቦት7 የአውሮፓ...(ከገጽ 2 የዞረ)

(ከገጽ 2 የዞረ)

በሀገሪቱ ውስጥ የሰፈነው የፓለቲካ አፈና እንዲያበቃ፤የፓለቲካ እሰረኞች እዲፈቱ ፤የፓለቲካው ምህዳር እንዲሰፋ እና የህግ የበላይነት እንዲከበር የሚጠይቅ ቅድመ ሁኔታ እንኳ ሳያታከልበት ይህን ሁሉ ገንዘብ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ መስጠት፣ በአውሮፓ ህብረት አገራት ውስጥ እንደ መሰረታዊ የሰው ልጅ መብት የሚቆጠሩት ነጻነትና ዲሞክራሲ ለኢትዮድያ ህዝብ አይገባውም የሚል የዘረኛነት አንድምታ የሚሰጥ ነው ብሎ ግንቦት 7እንደሚያምን መግለጫው አሰታውቆአል ።

በመቀጠልም: የ ኢትዮጵያ ህዝብ ከአለበት አሳፋሪ ድህነትና የተመጸዋችነት ልማድ በዘላቂነት ሊላቀቅ የሚችለው ነጻነቱና ሰብዓዊ ክብሩ በህግ ተረጋገጦለት ፣በአገሩ ሰርቶ መኖር ሲችል ብቻ ሰለሆነ የአውሮፓ ህብረት በድህነታችን ሽፋን ለነፃነት ያለንን ከፍተኛ ግምትና ፍቅር አሳንሶ መመልከቱን ማቆም አለበት ያለው የግንቦት 7 መግለጫ፣ እንዲህ አይነቱ እርዳታ መለስ ዜናዊ በኦጋዴንና በሱማሌ ውስጥ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ያደረሰውን አይነት ግፍና በደል እንዲሁም የጦር ወንጀል በመፈፀማቸው በአለም አቀፍ የሰብ ዓዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ለፍርድ እንዲቀርቡ የተከሰሱትን የአፍሪካ አምባገነን መንግስታት የልብ ልብ እንደሚሰጣቸው የአውሮፓ ህብረት ሊስተው አይገባም ካለ በኋላ ይዋል ይደር እንጂ አንዲህ አይነቱ ስህተት ከታሪክ ተወቃሽነትም አያድንም ብሏል ::

**በመጨረሻም ግንቦት7 የአውሮፓ ህብረት የእርዳታ ውሳኔውን እንዲያጤን እና የህብረቱ ሀገራትየኢትዮድያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ፤ለነጻነት እና ለሰብአዊ መብት መከበር ከሚያደርገው ትግል ጎን እንዲቆሙ ጥሪውን አስተላልፏል።**


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።